
# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ምዕራብ አጋማሽ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ደመናማ የአየር ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በምዕራብ ትግራይ እና በምዕራብ አማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ ኦሮሚያ እና በደቡብ ሶማሌ በአንዳንድ አካባቢዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ ከተፈጠሩ ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች በአንዳንድ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ. በላይ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በአይራ 31.8፣ ባአሶሳ 39.0፣ በአይከል 49.7፣ በባህር ዳር 39.5፣ በቤጊ 38.2 እና 38.0፣ በቻግኒ 33.3፣ በጎሬ 43.8 እንዲሁም በጠርቻ 31.6 በሚ.ሜ. ተመዝግቧል።


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-112 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ የምዕራብና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር፣ የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም እንዲሁም አዊ ዞን፤ ሁሉም ቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከሀዲያ፣ ስልጤና ከምባታ በስተቀር ሁሉም ዞኖች እንዲሁም ከኦሮሚያ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጥቂት የአርሲና ባሌ እንዲሁም የጉጂና ቦረና ዞኖች ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛ ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ ከአማራ የሰሜን ጎንደር ደቡባዊው ክፍል፤ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የአሶሳና የመተከል ሰሜናዊው ክፍል፤ ከጋምቤላ የጋምቤላ ዞን1 እና ዞን 3 ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ ወለጋ፣ የኢሉአባቦራ፣ የጅማና የጉጂ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)።


ካርታ 1  እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2  እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ነበር። ይህም በመሆኑም በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ መውጫው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ ቀደም ብለው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ፣ አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው። በሌላ በኩል በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች የነበረው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረ የታመናል። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ኦክቶበር 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ገፅታ ስንመለከት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በከፊል የምእራብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የደቡብ ምስራቅና የሰሜን ምስራቅ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ነበሩ፡፡ ይህንን ተከትሎ አብዛኛው የባሮ አኮቦ፣ የታችኛው አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦና ጥቂት የመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ጥቂት የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ የስምጥሸለቆ፣ የገናሌ ዳዋና ጥቂት የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደግሞ በአብዛኛው ከከፊል ደረቅ እስከ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ላይ ነበሩ (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2018 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህም ሌላ ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ከሚጠበቁት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተነሳ በተለይም በአንዳንድ የምዕራብና የደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም በጥቂት ደቡባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ ኪስ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ አርሲና ባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮ እና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ደጋህቡር፣ ፊቅ፣ ቀብሪደሃር፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ጎዴ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

## እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ
## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

ከላይ በትንበያው እንደተገለፀው በሚቀጥለው የኦክቶበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት ፍላጎት ከማሟላት አንፃር አወንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት በደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ

ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ብዙውን ጊዜ ደረቅ፣ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚጠበቅ በመሆኑ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ የሰሜንና የሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የበጋ ወቅታችው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም፤ ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ በተለያየ ሁኔታ ተገልብጠው በድጋሚ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚያሳይ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በምዕራባዊውና በደቡቡባዊ የሀገሩቱ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ትንበያው ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ቀናት የመካከለኛውና የታችኛው አባይ፣ የተከዜ፣ የኦሞ ጊቤ፣ የሪፍት ቫሊ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና የኦጋዴን ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አንዳንድ በደቡባዊ የገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በመጠን ከፍ ያለ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ትንበያችን ያመለክታል፡፡ በመሆኑ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በመሰብሰብ በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡